Arlington Public Schools

# የተማሪ ድጋፍ የድርጊት መርሃ ግብር

ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችና ጣልቃ ገብነት ለሚፈልጉ፡፡



## የተማሪ ድጋፍ የድርጊት መርሃ ግብር ስልታዊ ግቦች

### አካታችነት

ሁሉም አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የሚካተቱበት፣ የሚከበሩበትና ዋጋ እንዳላቸው የሚቆጠሩበት ማህበረሰብ መገንባት፣ የኮርስ ይዘትን እንዲያገኙ፣ በመማር እንቅስቃሴዎች ላይ ሙሉ በሙሉ እንዲሳተፉ እንዲሁም እውቀታቸውንና ጥንካሬዎቻቸውን እንዲያሳዩ ያስችላቸዋል፡፡

### ልህቀት

ለሁሉም የአካል ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎች ፍትሃዊነትን የሚያረጋግጥ እራስን ማገዝና ተዛማጅ ስርአተ ትምህርትን በመጠቀም ለትርጉም እና ለአዋቂነት እንዲማሩ ማድረግ፡፡

### ፍትሃዊነት

በታሪካዊ ውክልና ለሌላቸው ቡድኖች የእድል ክፍተቶችን መቅረፍና በእያንዳንዱ የተማሪ ልዩ ፍላጎት ላይ መሰረት ያደረገ የመማር እድሎችን በመስጠት የላቀ ደረጃን ማግኘት፡፡

### ተደራሽነት

አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ተገቢው ድጋፍ ተደርጎላቸው በከፍተኛ ደረጃ ኮርሶች እንዲሳካላቸው በትልቁ ተስፋ ማድረግ፡፡

### መተባበር

የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ስኬት ለመደገፍ ከቤተሰቦች፣ ማህበረሰቡና ሰራተኞች ጋር ትብብር ማድረግ፡፡

በ2018-2019 የትምህርት አመት አርሊንግተን የህዝብ ትምህርት ቤቶች (APS) ከህዝብ አማካሪ ቡን (PCG) ጋር አጋር በመሆን የፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች እና ጣልቃ መግባት የሚያስፈልጋቸው ስኬታማነት እና ጥራት በአጠቃላይ በተመለከተ የፕሮግራም ክለሳ ሰርቷል፡፡ በክለሳው ማጠቃለያ የመጨረሻ ሪፖርት የተለቀቀ ሲሆን ለቀጣይ መሻሻሎች ጥንካሬዎች እና አስተያየቶች አካቷል በ2019 መጨረሻ APS ከPCG ጋር መስራት በመቀጠል አስተያየቶችን እውን ለማድረግ ማለትም መጨረሻ ሪፖርት ውስጥ ያሉን ለመተግበር የረጅም ጊዜ የድርጊት እቅድ ለማዘጋጀት የአጋርነት ስራዎቹን ቀጥሏል፡፡ የሚከተለው የድርጊት እቅድ ከድርጊት እቅድ ሂደቶች የተገኘ ውጤት ነው፡፡

የድርጊት መርሃ ግብሩ ከክፍል ስልታዊ እቅድ ጋር በሚጣጣሙ እና በድርጊት መርሃ ግብሩ ውስጥ እንዲካተቱ ለተደረጉ ተግባራት ራዕይን በሚያቀርቡ ቁልፍ ስልታዊ ግቦች የታገዘ ነው፡፡ እቅዱ የሚያካትቱ 4 ዋነኛ አርእስታዊ ቦታዎች ሲኖሩ እነሱም የአርሊግተን የድጋፍ ተፈጻሚ ሲስተም፣ ልዩ ትምህርት፣ ክፍል 504 እንዲሁም ድርጅት እና ስራዎች ናቸው፡፡ እያንዳንዱ አርስት ቦታ ስራውን የሚመሩ ቁርጠኝነቶች፣ የስራ ብቃት አመላካቾች APS ስላለው ቁርጠኝነት የሚገልጹ እና ስልቶች እንዴት ቁርጠኝነቶች እውን ማድረግ እንደሚቻል ያካትታሉ፡፡ የሁሉም ድርጊት እቅድ ሂደት በመደበኛነት ቁጥጥር ተደርጎበት በሰነድ የሚያዝ ሲሆን ውጤቱም ለማህበረሰቡ የሚገለጽ ይሆናል፡፡

PUBLIC CONSULTING GROUP



# ልዩ ትምህርት

## የእኛ ቁርጠኝነቶች

ይህን እናደርጋለን…

- ለጥራት ያለው ትምህርት መልካም አጋጣሚዎች ቀርቤታ በመስጠት ለተማሪዎች ገደብ ያለበት ሁኔታ ውስጥም አገልግሎት መስጠት፡፡
- ተማሪዎች ያላቸው ፍላጎቶች በግል ትምህርት ፕሮግራም (IEP) ለሁሉም ባለ ድርሻዎች ማሳወቅ፡፡
- ለሁሉም ተማሪዎች ዝቅተኛ የሚገደብ አካባቢ (LRE) ማግኘት እንዲችሉ የአገልግሎት አቅርቦት ሞዴል ሰርቶ መተግበር፡፡
- በሰራተኞች፣ ቤተሰብ እና ማህበሰረቡ መካከል ቀጣይ፣ ህጋዊ እና የሁለት መንገድ ግንኙነት መጠቀም ናቸው፡፡

## የውጤት አመላካቾች

1. አካል ጉዳተኛ የሆኑ ተማሪዎች ቢያንስ 80% ያላቸውን 80% ወይም ከዛ በላይ የትምህርት ቤት ቀን አጠቃላይ ትምህርት ውስጥ ያሳልፋሉ፡፡
2. አርሊግተን የህዝብ ትምህርት ቤቶች የስጋት-ጥመርታ 1.0 በታሪክ በዝቅተኛ ደረጃ የተወከሉ ቡድኖች በዝቅተኛ ገዳቢ አካባቢ/አካታች ውክልናዎች መካከል ይኖራቸዋል፡፡
3. አርሊግተን የህዝብ ትምህርት ቤቶች የእስቴቱ ኢላማ በልጆች ብዛት እድሜ 3-5 በግል ትምህርት ፕሮግራሞች (IEPs) መደበኛ የቅድመ ትምህርት ፕሮግራም ላይ ከፍ በማድረግ አብዛኛዎቹን ልዩ ትምህርት እና ተያያዥ አገልግሎቶች በትምህርት ቤት እድሜ በፊት ባለው ፕሮግራም የሚቀበል ይሆናል፡፡
4. በየአመቱ የተማሪዎች IEP 80% ግቦች በተማሪ በተገቢው መረጃ ተደግፎ እንዲወጣ ይደረጋል፡፡
5. ከተመረጡት ትምህርት ቤቶች 100% የሚሆኑት፣ በየዓመቱ፣ ልዩ የተነደፈ መመሪያ (SDI) በተማሪው IEP ጋር በተጣጣመ መልኩ በሁሉም የትምህርት ተቋማት በታማኝነት ይተገበራሉ፡፡
6. 100% የተመረጡ ፋይሎች የጎልደን ትሬድ ቴሬስ ሆልድ መስፈርት ያሟላሉ፡፡
7. ተማሪዎች ከመዋለ ህጻናጽ-5 በIEP ቢያንስ በPALS ባለ ልኬት አንድ ደረጃ ጠቀሜታ ያገኛሉ፡፡
8. በንባብ፣ በመጻፍ እና በሂሳብ የላቀ ብቃት ላለው ወይም የላቀ ውጤት ላመጡ ለእያንዳንዱ የይዘት አካባቢ IEP ያላቸው ተማሪዎች ስኬት ይጨምራል፡፡
9. ተማሪዎች IEP 6-8 በማንበብ እና ሂሳብ በማንበብ እንዲሁም ሂሳብ ቆጠራ ልኬት መሰረት ቢያንስ አንድ ደረጃ ከፍ ይላሉ፡፡
10. ከሚከተሉት የማጠናቀቂያ ውጤቶች በአንዱ ሲለካ ቁጥራቸው እየጨመረ የመጣ IEPs ያላቸው ተማሪዎች ከፍተኛ ደረጃ ኮርስ ያጠናቅቃሉ፡ የላቀ አቀማመጥ (3.0 ወይም ከዚያ በላይ)፣ ዓለም አቀፍ ባካሎሬት (4.0 ወይም ከዚያ በላይ)፣ ክብር/የተጠናከረ (የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውጤትን ማለፍ)፣ ጣምራ ምዝገባ (ለኮሌጅ ማለፊያ ክፍል)፣ የኢንደስትሪ ማስረጃ (የኢንዱስትሪ ምስክር ወረቀት ያግኙ)፡፡
11. ተማሪዎች በIEP በመዋለ ህጻናጽ ውስጥ በቨርጂኒያ መዋለ ህጻናት የማንበብ ፕሮግራም ልኬት መሰረት ቢያንስ አንድ ደረጃ ከፍ ይላሉ፡፡
12. አርሊግንተን የህዝብ ትምህርት ቤቶች እድሜአቸው 3-5 ለሆኑ ልጆች የተያዘን የእስቴቱን ብዛት ኢላማ በማህበራዊ -ስሜታዊ ክህሎት እውቀት እና ክህሎት መጠቀም እና ከሚጠበቅ እድሜ በታች ተገቢ ባህሪ እና በውስጣቸው ያለውን አሰራር ከመጠቀም አኳያ የተያዘለትን እቅድ ባለፈ መልኩ የሚያሳካ ይሆናል፡፡
13. አርሊንግተን ልዩ ትምህርት አማካሪ ኮሚቴ (ASEAC) የሚመጡ ሁሉም ክፍት/ህዝባዊ አስተያየቶች መፍትሔ ያገኛሉ ወይም በ 1 ወር ውስጥ ምላሽ ይሰጣሉ፡፡

## ስልቶች

- አካታች የሆነ አሰራርን ለመጨመር ግልጽ ራዕይ እና አጠቃላይ የረጅም ጊዜ እቅድ መፍጠር
- በ UDL አቀራረብ በዕድገት ጎራዎች እና መመሪያዎች ላይ አካታች የቅድመ መዋለ ህጻናት አማራጮች እና ሙያዊ ትምህርት ተደራሽነትን ማስፋት፡፡
- ገደቦች እና የማያካትቱ በተመለከተ መመሪያ በማውጣት ማዕከላዊ የመረጃ አሰባሰብ ማበልጸግ እና ስለ ተገቢ ስልቶች ስልጠና ማስፋፋት፡፡
- በልዩ ሁኔታ ተነድፈው የተዘጋጁ ትዕዛዞ የተማሪዎች የግል ፍላጎቶች ለመሟላት ማቅረብ፡፡
- የተማሪዎች የግምገማ ድጋፍ ምን ያህል አካል ጉዳተኝነትን መኖር እንደሚያካተት መተንተን እና አሁን ያለውን ያካዳሚክ ስኬት እና ተግባራዊ አፈጻጸም መግለጫ ግልጽ የሆነ ግንኙነት በማሳየት ፍላጎቶች ማካተት እና በትዕዛዞች እና ምዘና መኖሪያዎች መምረጥ(ጎልደን ትሬንድ)፡፡
- የመረጃ አሰባሰብ እና ትንታኔ የIEP ግቦች ሂደት በተማሪዎች እድገት ቅደም ተከተል ማውጣት፡፡
- የተመቻቸ IEP ሂደት ከተወሳሰቡ ስብሰባዎች መተግበር እና ከአማካሪ ግሩፖች ጋር አጋርነትን በመጨመር የወላጅ መገልገያ ማዕከል (PRC) የወላጅነት ስልጠናዎች በተማሪዎች ድጋፍ ሂደቶች ላይ መተግበር፡፡
- በማዕከላዊ ጽህፈት ቤት እና በትምህርት ቤት ደረጃዎች የልዩ ትምህርት ተጠያቂነት ጥበቃ መንገዶችን መወሰን፡፡
- የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ከፍ ባሉ ኮርሶች ላይ የሚኖር ምደባ ለመጨመር ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ጋር መስራት፡፡
- ለትምህርቱ ቤቱ መመሪያ፣ ስልጠኛ እና ድጋፍ ተገቢፕሮግራሞች እና ስልቶችን ለእጥፍ የተለዩ ተማሪዎች እንዴት መተገብር እንዳለበት እንዲረዱ ለትምህርት ቤቶች እነዚህን ስልጣናዎች መስጠት፡፡
- የ5-ዓመት እቅድን ለመደገፍ ከእንግሊዘኛ ተማሪዎች ጽህፈት ቤት ጋር ይተባበሩ እና የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችም የእንግሊዘኛ ተማሪ ለሆኑ ተማሪዎች የአብሮ የማስተማር ሞዴል ለመመስረት፡፡
- የተማሪዎች ድጋፍ አስተባባሪዎች (SSC) የግብይት ሂደት እንዲያስተዳድሩ እና በትምህርት ቤቶች መካከል 6ኛ እና 9ኛ ክፍል ተማሪዎች እውቅት እንዲጋሩ ማድረግ፡፡
- እኔ ቁርጠኛ ነኝ ሚለውን ፕሮጀክት መቀበል እና ያሉ ሀብቶችን ማስፋፋት ትርጉም ያለው የተማሪዎች ተሳትፎ IEP ስብሰባቸው ወቅት ማበረታታት፡፡
- ለተማሪዎች IEP እንዲያገኙ (በወላጅ ፈቃድ) ማቅረብ፡፡



# አርሊንግተን ደረጃ ያለው የድጋፍ ስርአት (ATSS)

## የእኛ ቁርጠኝነቶች

ይህን እናደርጋለን…

- በርካታ ንቁ የድጋፍ ሲስተም ከፍተኛ ጥራት ያለው መጀመሪያ ትዕዛዝ በተለዋዋጭ ሞዴል ጣልቃ መግባት እንደ ግል ተማሪ ፍላጎት መተግበር፡፡
- ቀጣይ የሆነ የተማሪ ድጋፍ ቡድን (SST) አግባብ በመላው ዲስትሪክቱ የጣልቃ መግባት ስልቶችን ለመተግበር እና ለመቆጣጠር የተማሪዎችን የአጠቃላይ ትምህርት ስኬት ከፍ ለማድረግ መጠቀም፡፡
- ሁሉም የአጠቃላይ ትምህርት ደረጃ ያላቸው የድጋፍ ስርአቶች ጥቅም ላይ ከዋሉ በኋላ የግምገማ ሂደቱን ተግባራዊ ማድረግ፡፡
- ከሁሉም አጠቃላይ ትምህርት ብቁ ሲስተም ድጋፍ በኃላ የግምገማ ሂደት መተግበር ችግሮች ያሉባቸው ተማሪዎች ካሉ ለግምገማ ለተገቢው መቅረባቸውን ለመወሰን መረጃውን መጠቀም፡፡

## የውጤት አመላካቾች

1. በእንግሊዘኛ ቋንቋ ጥበባት (ELA)፣ በሂሳብ እና/ወይም ማህበራዊ-ስሜታዊ ትምህርት (SEL) በአሳሽ የተጠቁ ተማሪዎች ከሌሎች ከሚቀበሏቸው አገልግሎቶች በተጨማሪ ቢያንስ አንድ ጣልቃ ገብነት ተለይተው ይታወቃሉ፡፡
2. በትምህርት ቤት ላይ የተመሰረቱ ሰራተኞች የሂደት መከታተያ መሳሪያን ቢያንስ በየሩብ አመቱ ለእያንዳንዱ የታወቁ ጣልቃገብነቶችን የሚያስተዳድሩ ይሆናል፡፡
3. ከመዋእለ ህጻናት-8 ክፍል ያሉ ተማሪዎች በ PALS እና/ወይም በንባብና በሂሳብ ቆጠራ ሲለካ ቢያንስ የአንድ አመት የንባብና የሂሳብ ጭማሪ ያገኛሉ፡፡

## ስልቶች

- ቀጣይ በሆነ መልኩ ATSS መመሪያ ሰነዶች ማብልጸግ እና የተማሪዎችን የድጋፍ ማኑዋል ማሻሻል፡፡
- ATSS የዲስትሪክ አመራር ቡድን መመስረት እና ቀጣይ የትምህርት ቤት መረጃ አመራር ቡድኖች፡፡
- የአካዳሚክ እና ማህበራዊ ስሜት ትምህርት በማጣራት (SEL) የጣልቃ መግባት መመሪያ እና የሂደት ቁጥጥር ለእያንዳንዱ የሚጠበቀውን ማጥራት፡፡
- አሁን ያለውን የይዘት ቦታ እቅዶች እና ሀብቶች UDL አውታር እና መርሆችን መጠቀም፡፡
- የመረጃ አሰባሰብ እና ትንታኔ ቅደም ተከተል በመውጣት ተማሪዎችን አካዳሚክ እድገት እና ማህበራዊ ቁጥጥር ማድረግ እና ማፋጠን፡፡



# ክፍል 504

ይህን እናደርጋለን…

- በክፍል 504 ላይ የተለዩ አሰራሮች ሂደቶች እና ፕሮቶኮሎች በማሻሻል ድጋፎች ተገቢ በሆኑ መልኩ መድረሳቸውን ማረጋገጥ፡፡
- ተማሪዎች 504 እቅድ የሚያስፈልጋቸውን በተመለከተ ለሁሉም ባለ ድርሻዎች ማሳወቅ፡፡

## የውጤት አመላካቾች

1. በእንግሊዘኛ ቋንቋ ጥበባት (ELA)፣ በሂሳብ እና/ወይም ማህበራዊ-ስሜታዊ ትምህርት (SEL) በአሳሽ የተጠቁ ተማሪዎች ከሌሎች ከሚቀበሏቸው አገልግሎቶች በተጨማሪ ቢያንስ አንድ ጣልቃ ገብነት ተለይተው ይታወቃሉ፡፡
2. በትምህርት ቤት ላይ የተመሰረቱ ሰራተኞች የሂደት መከታተያ መሳሪያን ቢያንስ በየሩብ አመቱ ለእያንዳንዱ የታወቁ ጣልቃገብነቶችን የሚያስተዳድሩ ይሆናል፡፡
3. ከመዋእለ ህጻናት-8 ክፍል ያሉ ተማሪዎች በ PALS እና/ወይም በንባብና በሂሳብ ቆጠራ ሲለካ ቢያንስ የአንድ አመት የንባብና የሂሳብ ጭማሪ ያገኛሉ፡፡

## ስልቶች

- በ 504 እና በጤና እቅዶች ላይ የመመሪያ ቁሳቁሶችን ማዘጋጀትና ተማሪዎች በትክክል መለየታቸውን ለማረጋገጥ በየአመቱ የእቅድ ናሙና መፈተሽ፡፡
- ከ 504 ብቁነትና የእቅድ ማረፊያ አጠቃቀም ጋር የተያያዙ አዝማሚያዎችን ለመለየት በየአመቱ የታማኝነት ፍተሻዎችን ማካሄድ፡፡
- በተማሪ ድጋፍና 504 ብቁነት ሂደት ምን እንደሚጠብቁ ለቤተሰቦች መመሪያ መፍጠር፡፡
- ለተማሪዎች የ 504 እቅዶቻቸውን (በወላጅ ፈቃድ) እንዲያገኙ ማቅረብ፡፡



# ድርጅቶችና ሰራዎች

## የእኛ ቁርጠኝነቶች

ይህን እናደርጋለን…

- ተባባሪ፣ ራዕይ ያለውና ግልጽ የሆነ አመራር መጠቀም፡፡
- የተማሪዎችን ፍላጎት የሚያሟላ እና ምርጥ ተሞክሮዎችን በአካታች ትምህርት ቤቶች የሚደግፍ የግብአት ድልድል ስርአት እንዲተገበር ማድረግ፡፡

## የውጤት አመላካቾች

1. እያንዳንዱ ትምህርት ቤት የ90 ቀኖች የሂደት እቅድ ቢያንስ ለአንድ ግብ የተለየ ለSOL ደረጃ 3 IEP ላሉት ተማሪዎች ስኬታ እና ከዛ በላይ ለሆኑ እና በአንድ ሌላ መደብ (የ PALS እድገት፣ የLRE ማሻሻያዎች፣ ወይም የግብ ማካበት) ወይም ግብር ማሳካት በአርሊግተን የ5 አመት የተማሪዎች ድጋፍ እቅድ መሰረት ተፈጻሚ ማድረግ፡፡
2. የአርሊግተን የህዝብ ትምህርት ቤቶች ትምህርት ቤት መሰረት ያደረገ የተማሪ ድጋፍ አስተባባሪዎች (SSC) በሙሉ ጊዜ እያንዳንዳቸው ለአንድ ትምህርት ቤት እንዲመደቡ ሙሉ ፈንድ ያቀርባል፡፡

## ስልቶች

- ይህ የድርጊት እቅድ ትግበራ እና ውጤቱን በየአመቱ ውጤት በማተም መቆጣጠር፡፡
- የ SSCs ሙሉ ማሟያዎችን ጨምሮ በ OSE የቀረበውን ደረጃ በደረጃ የሰው ኃይል እቅድ ማጠናቀቅ፡
- በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት የ90 ቀኖች የሂደት እቅድ ቢያንስ አንድ ግብ ለሁሉም ንዑስ ቡድን ህዝቦች መካተቱን ለመወያየት መሳተፍ፡፡
- ሀብት ምደባ ለማስቻል እና በርካታ የአመት ውስጥ ክፍፍሎች ለመፍጠር እና የእቅድ ሁኔታዎችን ለመከለስ መወሰን፡፡
- አካታች የገንዘብ ድጋፍ ሞዴሎችን ማዘጋጀት እና የፋይናንስ ተጽእኖን መተንተን፣ የፕሮግራም ግቦችን እና የፊስካል እውነታዎችን ለማመጣጠን የእቅድ ሁኔታዎችን መከለስ፡፡
- የአጠቃላይ ትምህርት እና የልዩ ትምህርት ተማሪዎችን ለመደገፍ ረቂቅ ፖሊሲ እና PIP ትራንስፖርትን መተግበር፡፡
- የግል ፕሮፌሽናል ትምህርት መንገድን ለሰራተኞች መፍጠር፡፡



## የእኛ ተልእኮ

ሁሉም ተማሪዎች በአስተማማኝ፣ ጤናማና ድጋፍ ሰጪ የትምህርት አካባቢዎች መማራቸውንና መበልጸጋቸውን ማረጋገጥ



## የእኛ ራእይ


ሁሉም ተማሪዎች ህልማቸውን እንዲያሳድጉ፣ እድሎቻቸውን እንዲፈልጉና የወደፊት ህይወታቸውን እንዲፈጥሩ የሚያስችል ሁሉን አቀፍ ማህበረሰብ መሆን

# የአርሊግተን ህዝብ ትምህርት ቤቶች ጎልደን ትሬድ መግለጫ

የግል ትምህርት ፕሮግራም (IEP) ቡድኖች የተማሪዎችን አካል ጉዳተኝነት ባላቸው የመማር ችሎታ እና አካል ጉዳተኛ ያልሆኑ ልጆች ከሚሰሩት ነገር አኳያ መረዳት እና ተማሪዎች ትምህርት ቤት ስለሚኖራቸው ስኬት መስመር መፍጠር ይኖርባቸዋል፡፡ ልጁ በዚህ አመት ወዴት እየሄደ ነው? እሱ ወይም እሷ በአካዳሚክ እና በተግባራዊ እድገት ምን ሊሰሩ ይችላሉ? የIEP ቡድን በአመቱ መጨረሻ ልጁ ምን ማሳካት እንደሚችል ይሰማቸዋል?

## ጎልደን ትሬድ ምንድን ነው?

- ለአካል ጉዳተኛ ተማሪ፣ ግምገማው የአካል ጉዳተኞችን መኖር የሚደግፍ እና አሁን ካለው የአካዳሚክ ስኬት እና የተግባር አፈጻጸም (PLAAFP) ደረጃዎች መግለጫ፣ የተማሪ ባህሪያትን፣ የማካተት ፍላጎቶችን እና የተመረጡ ማመቻቻዎችን ለትምህርት እና ለግምገማ የሚያቀርብ መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበትየእሱ ወይም የእሷ የግለሰብ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ቡድን፡፡
- ጎልደን ትሬድ በመባል በሚታወቀው የማስረጃ አካል በኩል ያለው ይህ አመክንዮአዊ እድገት የተማሪውን የተሟላ ትምህርታዊ ታሪክ ለመንገር የተለያዩ ክፍሎቹን ማገናኘት አለበት፡፡




### ግምገማ

ለመማር የተማሪዎች ባህሪያት ምንድን ናቸው? በሰነድ የተያያዘ የእሱ/እሷ አካል ጉዳት ምንድን ነው?

### የወቅቱ ደረጃዎች

የተማሪው የአካዳሚክ ስኬት እና ተግባራዊ እቅድ የወቅቱ ደረጃ (PLAAFP) ምንድን ነው?ለክፍል ደረጃ ከአካል ጉዳት ወይም የቋንቋ መሰናክል ውጪ እንዴት ማግኘት ይቻላል?

### ሊለኩ የሚችሉ አመታዊ ግቦች

በአንድ አመት ውስጥ ጁ ማሳካት የሚጠበቅበት ምን ይሆናል? ከተማሪዎች ከክፍል ደረጃቸው አንጻር ያላቸው ብቃት ምን አይነት የትዕዛዝ ስራዎች ይጠበቃሉ? ግቦች ምክንያታዊ በሆነ መልኩ ጥብቅ እና ሊደረስባቸው የሚችሉ እና ሁሉንም የችግር አካባቢዎችን መፍታት የሚሉ ናቸው?

### መስተንግዶዎችና ለውጦች

እንደ ቤት እና ማህበረሰብ፣ በርካታ ነገሮች ለመማር ምን አይነት መስተንግዶዎች ያስፈልጋል? በሁሉም መልኩ ተማሪዎች እድገት እንዲኖራቸውም ምን አይነት አገልግሎቶች እና ድጋፎች ያስፈልጋሉ? መስተንግዶዎች በሰነድ የተመዘገቡ እና ለክፍል ትምህርት እና ግምገማ መሰረት ሆነው ያገለግላሉ? ተማሪው መጠለያውን በቋሚነት ለመጠቀም ፈቃደኛ መሆኑን ያሳያል?

### የሂደት ሪፖርቶች


ስለ IEP ትግበራ ምን አይነት መረጃዎች ተሰብሰበዋል የተማሪዎች ሂደት IEP ግቦችን ለማሳካት ችለዋል? ተማሪው እድገትን እያሳየ ነው?

# የአርሊንግተን የሕዝብ ትምህርት ቤቶች አጭር አለመመጣጠንና የአደጋ ጥምርታ መግለጫ

እንደ የተማሪ ድጋፍ የድርጊት መርሃ ግብር አካል፣ የአርሊንግተን የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ከሌሎች አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ጋር ሲነጻጸሩ በታሪክ ከመጠን በላይ ውክልና ካላቸው ዘር/ብሔረሰቦች የተውጣጡ ተማሪዎች ምን ያህል ገዳቢ በሆኑ የትምህርት አካባቢዎች የመመደባቸውን አደጋ ለማስላት የአደጋ ጥምርታ ቀመርን እየተጠቀመ ነው፡፡

## የስጋት ጥምርታ ምንድን ነው?

- የአደጋ ጥምርታ የቁጥር ንጽጽር ነው፣ እንደ ጥምርታ ወይም አስርዮሽ፣ ለአንድ የተወሰነ ዘር ወይም ጎሳ ቡድን በአካባቢያዊ የትምህርት ኤጀንሲ (LEA) ውስጥ ያለው የተወሰነ ውጤት ሊያመጣ የሚችለው አደጋ እና በLEA ውስጥ ላሉ ሌሎች ልጆች ሁሉ ተመሳሳይ ውጤት አደጋ መካከል የሚገኝ ነው፡፡
- በLEA ውስጥ በአንድ ዘር ወይም ጎሳ ውስጥ ላሉ ልጆች የተለየ ውጤት ሊያመጣ የሚችለውን አደጋ በLEA (ንጽጽር ቡድኑ) ውስጥ ላሉ ሁሉም ዘር ወይም ጎሳ ላሉ ልጆች በማካፈል ይሰላል፡፡




## ይህ እንዴት ይሰላል?

ለትምህርታዊ ሁኔታየአደጋ ጥምርታ የተሰላው ተካፋይ (ለተጠቀሰው የዘር/የብሄረሰብ ቡድን የተለየ ምደባ ያላቸው የAPS ተማሪዎች መቶኛ) በአካፋይ (በዘር/በጎሳ ቡድን ውስጥ ላልሆኑ ተማሪዎች የተመደቡት የAPS ተማሪዎች መቶኛ)በማድረግ ነው፡፡ የአደጋው ጥምርታ ለእያንዳንዱ ዘር/ብሄረሰብ ከተጠቀሰው ምደባ አንጻር የሚሰላ ይሆናል፡፡

የተለየ የትምህርት ሁኔታየስጋት ጥምርታ ስሌት የሚያካትተው፡

- በአጠቃላይ የትምህርት ክፍል ውስጥ 80% ወይም ከዚያ በላይ የትምህርት ቀን ምደባ፣
- በአጠቃላይ ትምህርት ክፍል ውስጥ ቢያንስ 40% እና ከ 79% ያልበለጠ የትምህርት ቀን፣
- በአጠቃላይ የትምህርት ክፍል ውስጥ ከ 40% ያነሰ የትምህርት ቀን ምደባ፣ እና
- የትምህርት ምደባዎች በተለየ ሁኔታ፡፡

በአጠቃላይ፣ የ1.0 ስጋት ጥምርታ እንደሚያመለክተው ከተሰጡት ዘር ወይም ጎሳ የተውጣጡ ልጆች ከሁሉም ዘር ወይም ጎሳ ልጆች የተለየ ውጤት የማግኘት እድላቸው የበለጠ ወይም ያነሰ አይደለም (ለምሳሌ ይበልጥ ገዳቢ በሆነ ቦታ ውስጥ መመደብ)፡፡ የ 2.0 ስጋት ጥምርታ እንደሚያመለክተው አንድ ቡድን ያንን ውጤት ሊያገኝ የሚችልበት እድል ከሌሎች ልጆች በእጥፍ የሚበልጥ ነው፡፡ የ 3.0 የአደጋ ጥምርታ ሶስት እጥፍ ሊሆን ይችላል፣ ወዘተ፡፡

ለአርሊንግተን የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የተማሪ ድጋፍ የድርጊት መርሃ ግብር ስሌት የተሰራበት የአደጋ ጥምርታ የቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያችንን ጉልህ አለመመጣጠን ዘዴን ለመድገም ተብሎ የተነደፈ አይደለም፡፡ የዚህ ስሌት አላማ የትምህርት ምደባ ውሳኔዎች በተማሪዎች ዘር/ጎሳ ምን ያህል ተጽእኖ እንደሚኖራቸው ለመገምገም የቅርጻዊ መረጃ መስጠት ነው፡፡

## የስጋት ጥምርታ ለምን እናሰላለን?

ለበርካታ አስርት አመታት የተደረመየምርምር ሰነድ እንደሚያመለክተው ከተወሰኑ ዘር/ብሄረሰቦች የተውጣጡ ተማሪዎች፣ በተለይም ጥቁር/አፍሪካዊ አሜሪካዊ ተማሪዎች፣ በልዩ ትምህርት ፕሮግራሞች ያልተመጣጠነ ውክልና ያላቸው እንዲሁም ከፍተኛ የእገዳ እና የመባረር እና የትምህርት ሁኔታዎችን የሚገድቡ ናቸው፡፡ የስጋት ጥምርታ ይህንን መረጃ መቆጣጠሪያ አንዱ መንገድ ነው፡፡

የአካል ጉዳተኛ ግለሰቦች የትምህርት ሕግ (IDEA) ስር፣ እያንዳንዱ LEA አካል ጉዳተኛ ልጆች እንደሆኑ በመለየት፣ በልዩ የትምህርት አካባቢዎች ውስጥ ያሉ ልጆችን ምደባና የድርጊቱን ክስተት፣ የቆይታ ጊዜና የስነምግባር እርምጃዎችን በተመለከተ እያንዳንዱ LEA በዘር/በጎሳ ላይ የተመሰረተ ጉልህ አለመመጣጠን እንዳለው ለመወሰን ይጠበቅባቸዋል፡፡ በስቴቶች ከላይ ያለውን ስጋት ጥምርታ በእያንዳንዱ መደብ ስለ ምደባ ተገቢ አለመሆን ያለውን ደረጃ የጠበቀ ዘዴ መጠቀም ይኖርባቸዋል፡፡

# አርሊግተን የህዝብ ትምህርት ቤቶች የስቴት ውጤት እቅድ (SPP) አመላካቾች መግለጫ

የግለሰብ አካል ጉዳተኞች ትምህርት ህግ (IDEA) እያንዳንዱ ግዛት በስቴት ደረጃ መረጃ እና የግለሰብ የትምህርት ቤት ክፍል ደረጃ መረጃን ለሕዝብ ሪፖርት እንዲያደርግ እና ግዛቱ እና ክፍሎቹ የስቴት ዒላማ እንዳገኙ ሪፖርት እንዲያደርግ በግዛቱ ልዩ ትምህርት የስቴት አፈጻጸም እቅድ/አመታዊ የስራ አፈጻጸም ሪፖርት ላይ ሪፖርት እንዲያደርግ ይጠይቃል፡፡ የትምህርት ቤት ክፍሎች ለሪፖርት፣ ክትትልና ተገዢነት አላማዎች መረጃና ዳታ እንዲያቀርቡ ይጠበቅባቸዋል፡፡

## SPP አመላካቾች ምንድን ናቸው?

- SPP አመላካቾች በአንድ መልኩ እስቴቱ ያላቸውን ውጤት አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች መለካት እና በይፋ ሪፖርት ማድረግ ናቸው፡፡
- ሁሉም የአካባቢ ትምህርት ኤጀንሲዎች (LEAs) ለSPP አመላካቾች ለግዛታቸው በየአመቱ መረጃ መስጠት ይኖርበታል፡፡ እነዚህ መረጃዎች ጥቅም ላይ የሚውሉት የእያንዳንዱ LEA ሁኔታ መከበር ለመወሰን እና በበርካታ ጉዳዮች LEA ለእስቴቱ አመታዊ የቁጥጥር ሂደት ተሳትፎ ለመምረጥ ነው፡፡
- SPP አመላካቾች በ 2 ምድቦዎች ይለያሉ፡
    - **ማክበር አመላካቾች** በተገለጸው ስቴት/ዲስትሪክት ያለን መከበር ከIDEA ደንቦች ጋር በማነጻጸር ይለካል፡፡
    - **የውጤት አመላካቾች** አካል ጉዳተኛ የሆኑ ተማሪዎች አፈጻጸም ይለካል፡፡
- እስቴቱ አመታዊ የውጤት ሪፖርት (APR) በአመላካቾች ሂደትን የሚያጠቃልል በእያንዳንዱ አመት ለፌዴራል መንግስት መስጠት ይኖርበታል፡፡

## SPP አመላካቾች እንዴት ተገኙ?

- የግለሰብ አካል ጉዳተኛ ሰዎች ትምህርት ህግ (IDEA) በ 2004 እንደገና ሲፈቀድ እስቴቱ በሚከተሉት ላይ ውጤት ለመለካት የቁጥር እና የጥራት አመላካቾች መጠቀም እንዳለበት አስቀምጧል፡
    1. ነጻ ተገቢ የሕዝብ ትምህርት (FAPE) ቢያንስ ገዳቢ አካባቢ አቅርቦት፡፡
    2. አጠቃላይ ቁጥጥር፣ ልጅ መፈለግ፣ ውጤታማ ክትትልን፣ የመፍትሄ ሃሳቦችን መጠቀም፣ ሽምግልና እንዲሁም የሽግግር አገልግሎት ስርዓትን ጨምሮ ስቴቱ ይህን ያካሂዳል፡፡
    3. ውክልናው ተገቢ ያልሆነ የመለየት ውጤት እስከሆነ ድረስ በልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች ውስጥ የዘር እና የጎሳ ቡድኖች ተመጣጣኝ ያልሆነ ውክልና፡፡
- በነዚህ ደንቦች መሰረት የልዩ ትምህርት ፕሮግራም ፌዴራል ጽህፈት ቤት (OSEP) ስቴቶችን አንዲመራ 17 አመላካቾች ለIDEA ትግበራቸው የተለየ ሲሆን ለOSEP ያላቸውን ሂደት እና ውጤት እንዴት ሪፖርት ማድረግ አንዳለባቸው ያካትታል፡፡ ስቴቶች የስብሰባ መስፈርቶች፣እገዛ ማስፈለግ ጣልቃ መግባት ፍላጎቶች ወይም ተገቢ ጣልቃ መግባት ፍላጎቶች እንደ ነበራቸው ማክበር እና በእያንዳንዱ አመላካች በሚኖር እድገት ላይ ይወሰናል፡፡ ይህም OSEP ተገቢ መረጃ ለኮንግሬስ ሪፖርት እንዲያደርግ እና እያንዳንዱ እስቴቱ መቆጣጠር እንዲችል ያስችለዋል፡፡ የቨርጂኒያ ትምህርት ክፍል (VDOE) በተጨማሪም ለትምህርት ቤት መምሪዎች አመታዊ የውሳኔ ውሳኔታዎች ይመድባል፡፡

## ውጤት መር ያደረገ ተጠያቂነት ምንድን ነው?

የስኬታ እና የምርቃት መጠን ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ለበርካታ አመታት ዝቅተኛ የሆነ ሲሆን ለ2012 OSEP የተጠያቂነት ሲስተሙን የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የተሻለ ውጤት ማሳካት ላይ እንደገና አተኩሯል፡፡ ይህ አዲስ አግባብ ውጤት መር ተጠያቂነት ሲባል በአጭሩ RDA ተብሎ ይጠራል፡፡

በእያንዳንዱ እስቴቱ እና የትምህርት ቤት መምሪዎች አካል ጉዳተኛ ልጆች ውጤት ለማሻሻል RDA አግባብ መጠቀም አሁን አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ምን የተሻለ ውጤት ማሳካት ይፈልጋሉ፡፡ እነዚህን ውጤቶች ለማምጣት ምን ድርጊት መፈጸም አለበት የሚለው ላይ ያተኩራል፡፡ የተሰበሰበው የ SPP አመልካች መረጃ አሁን ላይ OSEP ወደ RDA ማዕቀፍ በመሸጋገሩ ተጨማሪ ጠቀሜታ ያለው ሲሆን ለዚህም ምክንያቱም ከሁለቱም የተከታታይ ማትሪክስ እና የውጤት ነባር ተጠያቂነት ማትሪክስ ጋር የተያያዙ የደረጃ አሰጣጥ ነጥቦች አሉ፡፡

# SPP አመላካቾች ምንን ይለካሉ?

- **አመላካች 1 ምርቃት :** በIEPs ውስጥ ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በመደበኛ ዲፕሎማ የተመረቁ ተማሪዎች በበመቶኛ፡፡

- **አመልካች 2 ማቋረጥ፡፡** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን የሚያቋርጡ IEP ካላቸው ወጣቶች በመቶኛ፡፡

- **አመላካች 3A-C የእስቴቱ ምዘናዎች፡፡** በእስቴቱ ምዘናዎች ውስጥ IEP ልጆች ተሳትፎ እና ውጤት፡፡

- **አመላካች 4 ስነ ስርዓት፡፡** የእገዳ እና መባረር መጠን፡፡

- **አመላካች 5 5A-C የትምህርት አካባቢ እድሜ 6-21፡፡** በትምህርት አካባቢ የተሳተፉ እድሜያቸው ከ6-21 የሆኑ IEP ያላቸው ልጆች በመቶኛ፡፡

- **አመላካች 6A-B የትምህርት አካባቢ እድሜ 3-5፡፡** IEP ውስጥ ልጆች እድሜ 3-5 ፕሮግራም በመቶኛ፡፡

- **አመላካች 7A-C የቅድበ ትምህርት ቤት ውጤቶች፡፡** በIEP ውስጥ የቅድመ ትምህርት ቤት ልጆች እድሜ 3-5 ያሳዩት መሻሻል በመቶኛ፡፡

- **አመላካች 8 የወላጆች ተሳትፎ፡፡** በልዩ ትምህርት የሚያገኙ ልጆች ወላጆች በትምህርት ቤት የተመቻቸ የወላጅ ተሳትፎ አገልግሎት ለማሻሻል እና በአካል ጉዳተኛ ልጆች ውስጥ ሪፖርት ያደረጉ፡፡

- **አመላካች 9 በዘር/በጎሳ በተገቢው አለመወከል፡፡** ዲስትሪክቶች በዝርያ እና ጎሳ ልዩ ትምህርት ውስጥ እና ተያያዥ አገልግሎቶች ተገቢ ያልሆነ ውክልና መለየት፡፡

- **አመላካች 10 በተለየ አካል ጉዳት ተገቢ ያልሆነ ውክልና፡፡** ዲስትሪክቶች ውስጥ በዝርያ እና ጎሳ በተለየ አካል ጉዳት መደብ ተገቢ ያልሆነ ውክልና መለየት፡፡

- **አመላካች 11 ልጅ መፈለግ/ወቅታዊ ግምገማ፡፡** ልጆች የወላጅ ፈቃድ ባገኙ በ60 ቀኖች ውስጥ የመጀመሪያ ግምገማ ወይም እስቴቱ ባስቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት የተገመገመ በመቶኛ፡፡

- **አመላካች 12 ቅድመ ትምህርት ቤት ሽግግር፡፡** ከ 3 ዓመታቸው በፊት በክፍል C የተጠቀሱ፣ ለክፍል B ብቁ ሆነው የተገኙትና IEP በሦስተኛ የልደት ቀናቸው ተዘጋጅቶ ተግባራዊ የተደረገባቸው ልጆች በመቶኛ፡፡

- **አመላካቾች 13 ሁለተኛ ደረጃ ሽግግር፡፡** እድሜያቸው 16 እና ከዚያ በላይ የሆኑ IEP ያላቸው ከሁለተኛ ደረጃ በኋላ ሊለኩ የሚችሉ ግቦችን የተካተቱ ወጣቶች በመቶኛ፡፡

- **አመላካች 14A-C ድህረ ትምህርት ቤት ውጤቶች፡፡** ወጣቶች ሁለተኛ ትምህርት ቤት ውስጥ ያልሆኑ ትምህርት ቤቱ ሲለቁ IEP የነበራቸው እና በድህረ ትምህርት ቤት ፕሮግራሞች የተቧደኑ፡፡

- **አመላካች 15 አጠቃላይ ቁጥጥር፡፡** ወደ ውሳኔ ክፍሎች የሄዱ የመሰማት ጥያቄዎች በመቶኛ፡፡

- **አመላካች 16 IDEA ቅሬታዎች፡፡** የሽምግልና ስምምነቶችን ያስገኙ ሽምግልናዎች በመቶኛ፡፡

- **አመላካች 17 በእስቴቱ የተገኘ፡፡** የእስቴቱ SPP/APR የእስቴቱን ሲስተማቲክ የመሻሻል እቅድ (SSIP) የሚያካትት ሲሆን ይህ አመላካች መስፈርት ስለመሟላቱ የሚካተት ይሆናሉ፡፡